የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 11 እና 12

1. መጥምቁ ዮሐንስ በእስር ቤት ሳለ ደቀመዛሙርቱን ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የላካቸው ለምን ነበር?
 ሀ) ከእስር ቤት እንዲያስፈታው እንዲለምኑለት
 ለ) ደቀመዛሙርቱ በጌታችን ላይ ያላቸው እምነት እንዲጸና
 ሐ) ከኔ በኋላ ይመጣል ብሎ ትንቢት የተናገረለት እርሱ መሆኑን ለማጠየቅ
 መ) ለ እና ሐ
 ሠ) ሁሉም መልስ ናቸው

2. ጌታችን በዘመኑ የነበረውን ትውልድ በምን መሰለው?
 ሀ) በገበያ ተቀምጠው ጓደኞቻቸውን የሚጠሩ ልጆች
 ለ) የቀራጭና የኃጥአን ወዳጆች
 ሐ) ጋኔን ያለባቸው ሰዎች
 መ) መልሱ የለም

3. ጌታችን ኢየሱስ ብዙ ተአምራት አድርጎባቸው ነገር ግን በንስሐ ባለመመለሳቸው ከነቀፋቸው ከተሞች ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?
 ሀ) ቤተ ሳይዳ ለ) ኮራዚ ሐ) ቅፍርናሆም መ) ሰዶም

4. ፈሪሳውያን ጌታችንን ሊገድሉት የተማከሩት ስለምንድን ነው?
 ሀ) በሰንበት ፈውስን ስላደረገ
 ለ) ብዙ ሰዎችን ሳላዳነ
 ሐ) ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን መርጣለሁ ስላላቸው
 መ) ሁሉም መልስ ናቸው

5. "እነሆ፥ የመረጥሁት ልጄ፥ ነፍሴ የወደደችው፥ መንፈሴን በርሱ ላይ አኖራለሁ፤ እርሱ ለአሕዛብ ፍርድን ይናገራል" ብሎ ስለጌታችን ትንቢት የተናገረው ነቢይ ማን ነው?
 ሀ) ኢሳይያስ ለ) ዳዊት ሐ) ሰሎሞን መ) ኤርምያስ

6. የማይሰረይ ኃጢአት ብሎ ጌታችን ያስተማረው ምንን ነው?
 ሀ) ዝሙትን ለ) መንፈስ ቅዱስን መሳደብን ሐ) ሰው መግደልን መ) ሁሉም መልስ ናቸው

7. በምዕራፍ 13 ላይ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዮናስ እና ከሰሎሞን የሚበልጥ በዚያ እንዳለ የተናገረው ስለማን ነው?
 ሀ) አብረውት ስላሉት ደቀመዛሙርት
 ለ) ስለተከተለው ሕዝብ
 ሐ) ስለ ራሱ
 መ) በዘመኑ ስለሚነሳው ነቢይ

8. ከሚከተሉት ውስጥ በፍርድ ቀን ይህን ትውልድ ይፋረዳሉ ተብሎ የተነገረላቸው የትኞቹ ናቸው?
 ሀ) ንግሥተ ሳባ ለ) የነነዌ ሰዎች ሐ) የሲዶና ሰዎች መ) ሀ እና ለ ሠ) ሁሉም መልስ ናቸው

9. ምልክትን ይሻል የተባለውን ትውልድ የሚገልጸው የቱ ነው?
 ሀ) ዐመፀኛ ለ) ማመን የሚፈልግ ሐ) አመንዝራ መ) ሀ እና ሐ ሠ) ሁሉም መልስ ናቸው

10. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጋኔን ያደረበትን ዕውርና ደንቆሮ እስኪያይና እስኪናገር ድረስ በፈወሰው ጊዜ ሕዝቡ ምን ብሎ አደነቀው?
 ሀ) "ይህ የዳዊት ልጅ አይደለምን?"
 ለ) "በአጋንንት አለቃ በብዔል ዜቡል ነው እንጂ ይህስ አጋንንትን አያወጣም።"
 ሐ) "በእውነትም የእግዚአብሔር ልጅ ነው።"
 መ) ሀ እና ለ

11. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "እውነት እላችኋለሁ፥ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከእርሱ የሚበልጥ አልተነሣም" ብሎ የመሰከረው ስለማን ነው?
 ሀ) ስለ ራሱ
 ለ) ስለ መጥምቁ ዮሐንስ
 ሐ) ስለ ሕዝቡ
 መ) ስለ ደቀመዛሙርቱ

12. ጌታችን የሚያሸክመን ቀንበር እና ሸክም ምን አይነት ነው?
ሀ) ደካማ የሚያደርግ ሸክም
ለ) ከባድ ሸክም
ሐ) ቀንበሩም ልዝብ ሸክሙም ቀሊል
መ) ምንም ሸክም አያሸክመንም

13.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሸክማቸው የከበደ ምን እንዲያረጉ ነው የተናገረው?
ሀ) ወደ እርሱ እንዲመጡ
ለ) ሸክማቸውን እንዲችሉት
ሐ) ሸክማቸውን በራሳቸው እንዲያቀሉ
መ)ሁሉም

14.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሕዝቡ ጋር በመብላቱና በመጠጣቱ ምን ብለው ሰደቡት?
ሀ) በላተኛ እና የወይን ጠጅ ጠጪ
ለ)የቀራጮች ወዳጅ
ሐ)የኃጢአተኞች ወዳጅ
መ)ሁሉም

15.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እጁ የሰለለችውን ሰው በየት አዳነው?
ሀ) በቤተመቅደስ ለ) በምኩራብ ሐ) በበረሃ መ) በገዳመ ቆሮንቶስ

16.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰንበት ምን እንድናረግ አስተማረን?
ሀ) ከተቀመጥን ሳንነሳ ከዘረጋን ሳናጥፍ እንድውል
ለ) ክፉውን እንድናረግ
ሐ) መልካሙን እንድንሰራ
መ) ሁሉም

17.በማቴዎስ ወንጌል 11 “ዮሐንስ ሳይበላና ሳይጠጣ መጣ" ሲል ጌታችን ምን ማለቱ ነው?
ሀ)መጥምቁ ዮሐንስ ምንም ምግብ አይበላም ነበር
ለ) መጥምቁ ዮሐንስ አንበጣና የበረሃ ማር ይመገብ ነበር እንጂ ሌሎች ቅንጡ ምግቦች አይመገብም ነበር
ሐ) መጥምቁ ዮሐንስ ሁሉንም አይነት ምግብ ይመገብ ነበር
መ) ሁሉም

18.በትንቢተ ሆሴዕ 6፥ 6 "ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን፥ ከሚቃጠልም መሥዋዕት ይልቅ እግዚአብሔርን ማወቅ እወድዳለሁና።" የሚለውን ቃል ጌታችን ምን ለማስተማር ተጠቀመበት?
ሀ) ፈሪሳውያን ሐዋርያት ላይ መፍረድ እንደሌለባቸው
ለ) እግዚአብሔር ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን እና ፍቅርን እንደሚያስበልጥ
ሐ) መሥዋዕት ማቅረብ እንደማያስፈልግ
መ)ሀ እና ለ

19.የሰንበት ጌታ ማነው ?
ሀ) መላእክት ለ)እንስሳት ሐ) የሰው ልጅ መ)ሁሉም

20. በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 12 ላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል" ሲል ምን ማለቱ ነው?
ሀ) ሁሉም የሰው ልጅ በሞተ በሶስተኛው ቀን ይነሳል
ለ) ኢየሱስ ክርስቶስ በመቃብር 3 ቀን 3 ሌሊት ተቀብሮ ይቆያል
ሐ) ሁሉም ሰው ምልክት ማየት ከፈለገ 3 ቀን መተኛት አለበት
መ) ሁሉም ሰው በምድር ሆድ ውስጥ 3 ቀን 3 ሌሊት ከቆየ ተዓምር ማድረግ ይችላል